ኢትዮሚዲያ

## ርእሰ አንቀፅ

### ትርጉም ሀጎስ ሀብቶም

## አዲስ ሕግ አስከባሪ ወደ ከተማ እየዘለቁ ነው

እናንት መደዴ በየቦታው ቁጭ ቁጭ ያላችሁ አምባገነኖች፡ ኃይለኛ የለውጥ ነፋስ በአገረ አሜሪካ እየነፈሰ ነውና፡ ልብ አድርጉ! ስማቸው ባራክ ኦባማ የተሰኙ፡ አዲስ የሕግ አስከባሪ ወደ ከተማው እየገቡ ነው። ስድስት-ጎራሽ መትረየስ አይሸከሙም፤ መጻህፍተ-ህግ እንጂ። እንዲህ የሚል ህጉንም ለዓለሙ ሁሉ አምባገነኖች እየደነገጉ ነው፡ "አደብ ግዙ፡ ያለበለዚያ በባራክ ህግ ትሸነቆጣላችሁ። ይሄ ህግም ለስርአተ አልበኛው መለስና ለቅጥረኞች ለነፍሰ-ገዳዮችና ቀማኛ ባንክ ዘራፊዎችንም ይመለከታል።"

በላፈው ሰሞን ባራክ ዴሞክራቲክ ፓርቲውን በመወከል ለፕሬዚዳንት እጩ ተወዳዳሪ ሆነው ሲያሸንፉ ሁሉንም ወራዳ አምባገነኖችን ለማስጠንቀቅ የተናገሩት ቃል።

> "ለውጥ እውን እየሆነ ነው። የዘመኑን ስጋት ለመቋቋም የሚያስፈልገው የእኛ ጉልበትንና ነበልባል የሚተፋ መሳሪያ ሳይሆን የዲፕሎማሲ ኃይል ጥንካሬና ቀጥተኛነት ነው። መደዴ አምባገነኖች መንግሥታት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ያለምንም ፍርሃት የሀገራቸውን አቋም በየቦታው ላሉ አንባገነኖች ማሳውቅ አለባቸው። አንዴ እንደገና ነጻውን ዓለም የምንመራበት ወኔውና ትጋቱ ሊኖረን ይገባል። ያ ነው የሮዝቬልት፡ የትሩማን እና የኬኔዲ ውርስ። ያንን ነው የአሜሪካ ሕዝብ የሚፈልገው። ያ ነው ለውጥ ማለት።"

በርግጥ ባራክ የሚቀጥለው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ከመሆናቸው በፊትና፡ እንዲሆን እንጸልያለን እናምናለንም፡ የዱርየው መለስ ቡድን ጀንበር ሳትጠልቅበት "ድራሻቸው መጥፋት አለበት።" እስኪ **44**ኛውን የአሜሪካ ፕሬዚደንት፡ ባራክ ኦባማን እናስባቸው።

እናንተ መደዴ አምባገነኖች፡ አሜሪካ የቆመችው ለነጻነት፡ ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መርሆች ነው!

ባራክ ኦባማ "አሜሪካ የትና ለምን እንደቆመች" ሲናገሩ፡ ደም በጠማቸው ርካሽ፡ በጥባጭና ዘራፊ የአምባገነኖች ቡድን በተሞላችው ዓለም ውስጥ፡ የአሜሪካንን የውጭ ጉዳይ መርሆች የሚቀይሱትን የዴሞክራሲ፡ የነጻነት እና የሰብአዊ መብት መርሆች መናገሩ ነው። በሀምሌ**1996** ዓ.ም ባራክ ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፤

> "በያንዳንዱ የዓለም ክፍል፡ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን የአሜሪካንን ጥንታዊ መርሆች፡ ማለትም ዴሞክራሲን ሰብአዊ መብትንና ነጻነትን ማራመድ አለብን። ይሄ ከተቀረው ዓለም ጋር የምንጋራው ጥቅም ነው። በመጨረሻ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የሚያስፈልገንን ልብና እምሮ የሚገዛልንና የቀደመውን ተሰሚነታችንን የሚያስመልስልን። እንዲሁም የአሜሪካንን ባህልና አስተሳሰብ በዓለም ላይ የሚያስፋፋልን።" ሲሉ

በነሀሴ **1998** ባራክ ኦባማ ኬንያን ሲጎበኙ፡ የነቀዙ እንዲሁም ያዘገጡ የአፍሪካ መሪዎች ልክ እንደ ተስቦ ወረርሽኝ የህዝባችንን ሕይወት እያጠፉ ባለበት ሁኔታ ውስጥ፡ ዴሞክራሲና ነጻነት ሊኖር አይችልም በማለት ተናግረዋል።

> "ልክ እንደተቀሩት የአህጉሩ አገራት፡ ኬንያ ያልተሳካላት፤ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት ከሙስና የጸዳ የራሱን ህዝብ የሚያገለግል መንግስት መፍጠር ሂደቱ ላይ ነው። በከፍተኛ ጥንካሬ

ስለተዋጋችሁለት  ነጻነት የምናገረው፡ ዛሬ ያ ነጻነት አደጋ ላይ ስለወደቀ ነው። ሙስና እና የመሳሰሉት ነጻነትን ስጋት ላይ ከተውታል።”

በታህሳስ **1998** ዓ.ም፡ በ**60**ኛው የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት አዋጅ ምስረታ በአል ላይ፡ ባራክ አባማ፡ “ዓለም መርህ ያለው አዲስ  የአሜሪካ አመራር ትሻለች”  ይኸውም ሰብአዊ መብትን ነጻነትንና ዴሞክራሲን የሚያስጠብቅ አዲስ የአሜሪካ አመራር ትሻለች”  ብሏል።

“የዓለም  አቀፉ የሰብአዊ መብት አዋጅ፤ በዘመኑ ስር ነቀል ሰነድ ነበር። ምንም እንኳን ፍራንክሊን ደሩዝቬልት የዚያን ታሪካዊ ሰነድ  መጽደቅ ለማየት ባይታደሉም፡ የሱ “አራቱን ነጻነቶች”፡ ማለትም   ከመታደን ነጻ መሆንን ፤የንግግር ነጻነት፤ የሀይማኖት ነጻነት፤ ከችግርና ከፍርሀት ነጻ መሆን በሰነዱ ውስጥ  ተካተዋል። ያ አዋጅ የተወለደው ‘የናንተ ህመምና ውርደት የኔ ህመምና ውርደት”  ከሚል መርህ ነው። ላለፉት ሰባት ዓመታት  ፕሬዚደንት ቡሽ፡ ሩስቬልት ስለፍርሀት አጥፊነት የተውልንን ብልህ ምክርና የሞራል ብቃት ወደጎን በመጣል ክፍተት ፈጥረው ቆይተዋል  ። በሱዳን ዳርፉር ዘር ማጥፋት የተጨፈጨፉ በመቶሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተፈናቃዮች፤ በበርማ በድብደባ የተንሳቀሉ የቡድሀ እምነት መነኮሳት፤ የዚምባብዌ ፖለቲካ ተቃውሞ፤ በራሺያ የታሰሩ ነጻ ጋዜጠኞች፤ በፓኪስታን ቆራጥ ዳኞችና  የሰብአዊ መብት ጠበቆች፤ ወደማንኛው ዓለም አቤት እንደሚሉ ጨንቋቸዋል። በዚህ ሁሉ ምክንያት ዓለም አዲስ መርህ ያለው የአሜሪካ  አመራር ትሻለች”።
**ኢትዮጵያንም ከነዚህ ወደየትኛው ዓለም አቤት  እንደሚሉ ከቸገራቸው አገሮች ዝርዝር እንጨምራት።**

ባራክ  አባማን የተለየና ድንቅ የሚያደርጋቸው፡ የአሜሪካንን መሰራታዊ መርሆች አማላይ ኃይል እና የዘላቂ ሰነዳቸውን ዘላለማዊ ጠቀሜታ  በቅጡ መረዳታቸው ነው። ስለዚህም ባራክ አባማ ለጠባብ አምባገነኖች “የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ጥንታዊውን የአሜሪካ መርሆች  ያራምዳል”  የሚለውን መልእክት ሲያስተላልፉ፡ ለ”ግልጹ አለም”  የ**1776**ቱ የአሜሪካ የነጻነት አዋጅ   መጥቀሱ አሏቸው፤

“የሚከተለው  እውነታ፡ ማለትም የሰው ልጆች በተፈጥሮ እኩል መሆናቸውንና፡ ሁሉም በፈጣሪያቸው ማንም የማይነጥቃቸው መብቶች አሏቸው፤ እነዚህንም  የህይወት፤ የነጻነት እና ደስታቸውን የመከተል መብቶች ተጎናጽፈዋል፡ ይሄም ማስረጃ የማያስፈልገው ራሱን በራሱ የሚያረጋግጥ ሀቅ  መሆኑን እንቀበላለን። እነዚህን መብቶች ለማስጠበቅም ትክክለኛ ስልጣናቸውን ከህዝቦች ፈቃድ ያገኙ መንግስታት በሰዎች መካከል  ይቋቋማሉ። ማናቸውም ዓይነት መንግስትም እነዚህን መብቶች ሲሸረሽር፡ ያንን መንግስት መቀየር ወይንም ማስወገድ እንዲሁም ሌላ  መንግስት ማቋቋም የህዝብ መብት ነው…።”

እንደ  ፕሬዚዳንትም፡ በየቦታው ለተኮለኮሉት አምባገነን መንግስታት፡ የሚያስተላልፉት መልክት በአሜሪካ ሕገ-መንግስት መንፈስ፡ በነጻነት  እንደሚመሩ እየነገሯቸው ነው፤ “እኛ የአሜሪካ ህዝቦች፡ የላቀና ፍጹም ህብረት ለመፍጠር …  እንዲሁም የነጻነትን በረከትም  ለራሳችንና ለመጪው ትውልድ ለማረጋገጥ፡ ይህንን ሕገ-መንግስት አጽድቀን ለተባበረችው አሜሪካ መንግስታት እናጠናክራለን”  ባራክ መደዴ አምባገነኖች እንዲያውቁ የፈለጉት፤ በጌትስበርግ  ንግግራቸው እንዲህ ብለዋል፤ ሌላኛው የኢሊኖይስ ተወላጅ በአብርሀም ሊንከን እንደተማረኩና የሱንም ፈለግ እንደሚከተሉ ነው።  “የዛሬ አርባ ሰባት አመት በፊት አባቶቻችን በነጻነት ውስጥ የተጸነሰና ሁሉም የሰው ልጆች ሲፈጠሩ እኩል ናቸው ለሚለው መርህ  የቆመ፤ አዲስ መንግስት ፈጠሩ።”  ስለዚያ ነው ባራክ ኦባማ የሚናገሩት። ለሁሉም ስለሚገባ ነጻነት፡ በአምባገነኖች ፈቃድ  የተመሰረተ ሳይሆን በሕዝቦች ፈቃድ ስለተመሰረቱ መንግስታት፡ አብይ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሳይሆን፡ እግዚአብሄር የሰጠውን  የህይወት፡ የነጻነትና የንብረት መብት ስለመጠበቅ። እኩልነትና ፍትህ ለወንጀለኞች፡ ለሌቦችና ለቅጥረኞች ብቻ ሳይሆን፡ ለሁሉም።

## ባራክ ኦባማ ህመማችንንና ውርደታችንን ይረዳሉ

ባራክ ኦባማ ቋንቋችንን ይናገራሉ። ባራክ ኤች.አር **2003**ን እና በውስጡ የታቀፉትን መርሆች ይደግፋሉ።

በትክክል የሚሰማቸውን ነግረውናል፤ "የናንተ ህመምና ውርደት የኔም ህመምና ውርደት ነው" ብለውናል። ባራክ የአፍሪካውያንን፡ የኢትዮጵያዊያንን መሪር ስቃይ ሊረዱ በሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ የተቀመጡና ለነጻነት ያላቸውን ጥልቅ ምኞትና ጥማት የሚገነዘብ ብቸኛው ሰው ናቸው። ለአሜሪካም ላላቸው ራእይ፡ ጨካኝ አምባገነኖች የራሳቸውን ዜጎች የሚጨቁኑበትን ጉልበትና ወታደራዊ ጡንቻ በማጎልበት ሳይሆን፡ የአሜሪካንን አብይ መርሆች በመጠቀም የዓለምን ሕዝቦች ልቦናንና ሕሊና ማግኘት ነው።

እናንተ መደዴ አምባገነኖችና ቀጣፊዎች፡ ልብ ብላችሁ አድምጡ። በግድግዳ የተጻፈውንም አንብቡ። "የራሳችሁን ሕዝብ ማረድ፡ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሀን ዜጎችን ማሰር፡ የተቀናትን ሚሊዮኖችንም ማስራብ እስከቀጠላችሁ ድረስ፡ ባራክ በናንተ ተቃራኒ ይቆማል።" በራሳችሁ ሕዝብ ላይ ጦርነት ልታውጁና ጎረቤቶቻችሁን ልትፈጁ የሚያስችል ወታደራዊ እርጥባን ፍለጋ ወደ አሜሪካ ደጃፍ ስትዘልቁ፡ ባራክ ከበር ይመልሳችኋል። ህጋዊ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴን ያለርህራሄ እያጠፋችሁ፡ የፕሬስ ነጻነትን እየደመሰሳችሁ፡ የህግ አገዛዝን እየጣላችሁና፡ ዓለም አቀፍ ሕግጋትን እየጣሳችሁ ስለዴሞክራሲ የምታነበንቡትን የሀራጅ ሽያጭ ቋንቋ ባራክ አያዳምጡም። ባራክ፡ እናንተ አሜሪካንን በክልላዊ ጦርነት ልትተበትቧት፡ በምትፈጥሩት የጅሎች ሽብርተኞች ስጋት አይታለሉም። በአሜሪካ ስም ለማድረግ ለፈቀዳችሁት አላስፈላጊና አጥፊ ጦርነት የሚሰጣችሁ የውለታ ነጥብ የለም።

## ባራክ ለፕሬዚደንትነት ይመረጡ ዘንድ የማናደርገው ጥረት የለም

ባለፈው ግንቦት ባራክ እንዲህ ብልዋል፤ "አሜሪካ፡ ይሄ ሰዓታችን ነው። ይሄ ግዜያችንም ነው። ባረጁ ፖሊሲዎች ላይ ገጽ የምንገልጥበት፡ ለገጠመን ፈተና አዲስ ሀይልና አዲስ ሀሳቦች የምናመጣበት፡ ለምንወዳት አገራችን አዲስ አቅጣጫ የምናሳይበት፡ ሰዓት ነው።" ኢትዮጵያዊያን አሜሪካውያን፡ ይሄ የኛም ሰዓት ነው። በመደዴና ተልካሻ አምባገነኖች ላይ አዲስ ገጽ የምንከፍትበት ወቅት ነው። ለምንወዳት አገራችን አዲስ አቅጣጫ የምንቀይስበትና የምናረጋግጥበት ወቅት ነው። ይሄንን በባራክ እርዳታ እናደርገዋለን። ገንዘብ፡ ጊዜ፡ ጉልበት፡ እንዲሁም ድምጽ፡ የምንችለውን ሁሉ በሙሉ ስሜት እንስጣቸው።

## ይህ ለባራክ በጣም መልካም ከሆነ…

የአሜሪካው የነጻነት አዋጅ፡ ለኬንያ- አሜሪካዊ ለባራክ ኦባማ መልካም ከሆነ፡ ለኛ ለኢትዮጵያዊያን አሜሪካዊያንም እጅግ በጣም መልካም ነው። ልክ እንደ ባራክ ሁሉ፡ እኛም "የሰው ልጆች በተፈጥሮ እኩል መሆናቸውንና … እነዚህን መብቶች ለማስጠበቅም ትክክለኛ ስልጣናቸውን ከህዝቦች ፈቃድ ያገኙ መንግስታት በሰዎች መካከል መቋቋማቸውን … ማናቸውም ዓይነት መንግስትም እነዚህን መብቶች ሲሸረሽር፡ **ይሄንን መንግስት መቀየር ወይንም ማስወገድ እንዲሁም ሌላ መንግስት ማቋቋም የህዝብ መብት መሆኑን…** እናምናለን።"

እናንት መደዴ አምባገነኖች ኮርቻችሁን ተዘጋጁ፡

ጓዛችሁንም አንሱ፡

አዲስ የሕግ አስከባሪ ወደ ከተማ እየገቡ ነው በድንገት በገመድ እያነቃችሁ የጣላችሁት ፊሳ ሊነሳ ነው…